# ጋዜጣዊ መግለጫ

## በደቡብ ኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች የሚካሄድ ሀገራዊ የሽግግር ፍትህ የህዝብ ምክክርና የፖሊሲ ግብአት የማሰባሰብ ስራ መርሀ-ግብር መጠናቀቁን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን ለማርቀቅ በተጀመረው አገራዊ ትልም ማእቀፍ - በ'ሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አማራጮች' ሰነድ ላይ በክልሎች ደረጃ የሚካሄደውን ምክክር በመላው አገሪቱ በሚገኙ ከሀምሳ-ስምንት በላይ ከተሞች ከሚያዝያ እስከ ነሃሴ 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ለማከናወን መርሀ-ግብር መውጣቱ ይታወቃል።

በዚህ አግባብ የህዝብ ምክክሩ የመጀመሪያው ምእራፍ በኦሮሚያ ክልል አስራ ሶስት ከተሞች ከሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 5 ቀን 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በስኬት ተከናውኗል። ሂደቱ ቀጥሎም በሁለተኛው ምእራፍ ማእቀፍ በሲዳማ ብሄራዊ ክልል፣ በደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ብሄራዊ ክልል፣ እና በደቡብ ብ/ብ/ህ ብሄራዊ ክልል አስራ ሁለት ከተሞች (ሀዋሳ፣ ዲላ፣ አርባ-ምንጭ፣ ኮንሶ፣ ወልቂጤ፣ ቡታ-ጅራ፣ ወራቤ፣ ሆሳእና፣ ወላይታ-ሶዶ፣ ሚዛን፣ እና ቦንጋ) ከግንቦት 23 እስከ ሰኔ 10 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተካሂዷል።

እንደቀደመው ዙር ሁሉ በነዚህ የምክክር መድረኮች ላይም ፍጹም ገለልተኛ እና የሂደቱን ልዩ ግብ ታሳቢ ባደረገ ሂደት የተመረጡ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂ ግለሰቦች፣ የእምነት እና የማህበረሰብ መሪዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ አባላት፣ የወጣቶች እና ሴቶች ተወካዮች፣ እና የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ድምጽ የሚወክሉ ባለድርሻ አካላት በከፍተኛ ንቃት ተሳትፈዋል። በባለሙያዎች በቀረቡ አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች ላይ ጥልቅ ክርክር አካሂደዋል። ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን የማጠናከሪያ እና በአማራጭነት ሊያዙ የሚገቡ ምክረ-ሀሳቦችንም ተሳታፊዎቹ በሰፋት አቅርበዋል።

ከከተሞች እና ራቅ ካሉ አዋሳኝ ወረዳዎች የተጋበዘው ተሳታፊ በየመድረኮቹ ያለምንም መጓደል በመገኘት፣ እና በምክክር መድረኮቹ ላይም ከታቀደው በላይ ረጃጅም ሰአታትን በመጠቀም ያሳየው በባለቤትነት ስሜት የታጀበ ከፍተኛ ተሳትፎ - አሁንም ህዝቡ በሂደቱ ላይ ያለውን ጠንካራ እምነት ያሳየበት አጋጣሚ ሆኖ አልፏል። ለዚህም ከፍተኛ ክብር እና ምስጋና ይገባዋል።

በዚህ አጋጣሚ ከሰነዶች ዝግጅት ጀምሮ - በቦታዎች እና ተሳታፊዎች መረጣ፣ በሎጂስቲክስ እና በፋይናንስ ዝግጅት ለምክክር ሂደቶቹ ስራዎች አይነተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ አካላት ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

**የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን**
**ፍትህ ሚኒስቴር**
**ሰኔ 17 ቀን 2015 ዓ.ም**